SEPTEMBER 2021, VOLUME II



# FICDO

FIKIR INTEGRATED COMMUNITY DEVELOPMENT ORGANIZATION

ፍቅር የተቀናጀ የማህበረሰብ ልማት ድርጅት

SEPTEMBER 2021

# 2 YEAR ANNIVERSARY

## እንኳን አብሮ አደረሰን

**A MILLION THANKS FOR YOUR TRUST AND SUPPORT**

# CONTENTS

ይህንን መጽሄት በአማርኛና እንግሊዝኛ ለማቅረብ ተሞክሯል። ነገር ግን፤ በግዜ እጥረት ሁሉንም ገጾች መተርጎም አልቻልንም። በተጨማሪም፤ የእንግሊዝኛና የአማርኛው ይዘትና ሃሳብ ተመሳሳይ እንዲሆን ጥረት የተደረገ ቢሆንም፤ ቀጥታ ትርጉም አለመሆኑን አስቀድመን ማሳሰብ እንወዳለን።




5
**Message from the Board**
የቦርድ መልእክት

6
**A Year of Walking in Love: A Reflection**
የ2013 የፍቅር ጉዟችን

7
**Get to Know FICDO**

11
**Education Program**
የትምህርት ፕሮግራማችን

19
***SOUL-2-SOUL* Befriending Program**
"ፍቅር ለአረጋዊያንን"

23
**COVID-19 and Emergency Response**
የአስቸኳይ ግዜ እርዳታ ስራዎች

26
**Health Care Service**
የማህበረሰብ ጤና መድህን አገልግሎት

27
**Mobilization**
የማስተባበርና ማነቃቃት ስራዎች

34
**A Passion to Serve: *Interview with Founder of God's Mercy House***

37
**Join the Movement**
የፍቅር ጥሪ

38
**Critical Analysis of FICDO's Community Care**

SEPTEMBER 2021

መልካም አዲስ አመት




መልካም አዲስ አመት

# MESSAGE FROM THE BOARD

## የቦርድ መልእክት

Since FICDO started its operations in June 2019, we have been running social inclusion projects in Fitche town, Central Ethiopia. 2020/21 has been an exceptionally challenging year for everyone due to COVID-19. Hence, we needed to redouble our efforts to provide much needed service to vulnerable members of our community as much as we could. We mobilized our communities, the diaspora and friends from fields afar. We don't claim we have done everything perfectly, but we believe that we demonstrated practical love. Above all, we hope that we nurtured relationships and impassioned several kind-hearted people in our communities and elsewhere. I would like to thank all who stood by us during these tough times. Thank you for your trust, solidarity and friendship. You inspired us. Wishing you a happy New Year, we look forward to walking with you in our journey of love in the years ahead.

ፍቅር የተቀናጀ የማህበረሰብ ልማት ድርጅት (FICDO) ከተመሰረተበት ከ2011 ጀምሮ፤ በፍቼ ከተማ ማህበረሰብ-ተኮር ፕሮጀክቶችን በማከናወን ላይ ይገኛል። 2013 ግን ከCOVID-19 የተነሳ እጅግ ፈታኝ አመት ነበር። ከዚህ የተነሳ፤ ከባለፈው አመት በላይ፤ ያለ የሌለ አቅማችንን በማስተባበር በመሃከላችን ለሚኖሩ እና ለችግር ለተጋለጡ ብዙ ቤተሰቦች፤ ህጻናት እና አረጋዊያን ለመድረስ ሞክረናል። ብዙ ቢቀረንም፤ የከተማችንን ማህበረሰብ እና ድርጅቶች ለበጎ ስራ በማነሳሳት፤ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞችን ለማፍራት እና በጎነትን ለማበረታታት የተቻለንን ሰርተናል። ህብረተሰባችን በመተሳሰብ እንዲተሳሰር እና አንዱ ሌላውን እንዲያገለግል አበረታተናል፤ የፍቅር ዘር ዘርተናል። ከከተማችን ውጭ፤ በሃገር ውስጥና ውጭ ከሚኖሩ የኣካባቢው ተወላጆች እና ሌሎች ደጋፊዎቻችን ጋር ግንኙነት በመፍጠር ከማህበረሰባችን ጎን እንዲቆሙ ለማስተባበር ሞክረናል። በዚህ የበጎ ስራ ለተሳተፋችሁ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች፤ የከተማው ማህበረሰብ፤ ድርጅቶች፤ የመስተዳድር አካላት፤ ፍቅር ግድ ብሏችሁ ከኛ ጋር ለቆማችሁት በሩቅ እና በቅርብ ያላችሁ ደጋፊዎቻችን በድርጅቱና በራሴ ስም ከፍ ያለ ምስጋናና አድናቆቴን ልገልጥ እወዳለሁ። ያሳያችሁን ፍቅር ለበለጠ ስራ አነሳስቶናል። በአዲሱ አመትም በበለጠ መልካም ስራ አብረን እንድንቀጥል እያበረታታሁ፤ 2014 የሰላም፤የደስታና የፍቅር አመት እንዲሆንላችሁ በራሴና በድርጅታችን ስም እመኛለሁ።



Ayele Deneke, Chairperson, FICDO's Board of Directors
አየለ ደነቀ፤ የFICDO ቦርድ ሊ/መንበር

የFICDO ቦርድ አባላት፡
አየለ ደነቀ/ንጋቱ መረቀ/ ታደሰ ወልደማርያም(ዶ/ር) /አርቲስት አብርሃም ወልዴ/ ላቀው ረጋሳ/ የሻረግ ቸርነት
ሃይሉ ቶላሳ/ መሰረት ስዩም/ እውነቱ ኤርምያስ/ ካሰች ተስፋዬ / አርቲስት ትግስት ማሞ

# A YEAR OF WALKING IN LOVE

## *A Reflection*

## የ2013 የፍቅር ጉዟችን

In FICDO, we continually reflect on who we are as an organization, what we are doing and why we do what we do. Given that "serving and living out love" is at the heart of our mission, we believe that these reflective practices help us to internalize our organizational identity and stay on the right path. The work summarized in this magazine is just that - a reflection.

In a world where performance is measured in numbers and figures, our work may seem like a drop in an ocean given the huge demands in our communities. Yes, we have met the practical needs of some vulnerable people and showed unconditional love, but there is still much to do. However, we are sure of one thing; that our work is formative. i.e. through experiences, it develops understandings, nurtures relations and empowers individuals and communities, all of which may not be directly measured. We hope that we inspired our communities and you. We are certainly inspired by you, especially those who have committed to walking the journey of love with us despite having no immediate connection to the communities that we serve! We hope to continue to work together to inspire several others.

"ፍቅርን በተግባር መኖር እና በፍቅር ማገልገል" የአገልግሎታችን ዋና እንደመሆኑ መጠን፤ ስራችንን ለመገምገም ሁሉን በሚያየው ፈጣሪ ፊት ግዜ እየወሰድን ውስጣችንን እንፈትሻለን። ይኼም፤ ካለፈው እየተማርን፤ ስራችንን እያሻሻልን በመልካም ጎዳና እንድንራመድ ያግዘናል ብለን እናምናለን። የዚህ አመታዊ መጽሄታችን አንዱ አላማም ይኸው ነው።፡

በ2013፤ በማህበረሰባችን ውስጥ እገዛ እና ፍቅር ለሚያስፈልጋቸው ቀላል የማይባሉ ሰዎች በትክክለኛ ግዜ እንደአቅማችን ትክክለኛ እገዛ እንዳደረግን ቢሰማንም፤ በአካባቢያችን ካለው ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች አንጻር የኛ ስራ "ባህርን በጭልፋ" እንደመሞከር መሆኑን እንገነዘባለን። ነገር ግን፤ በFICDO ስኬትን በቁጥሮች እና በፐርሰንት አንመዝንም። ስራችን የመልካም ሰዎችን እና የማህበረሰቡን ልብ ለበጎ ስራ የሚቀሰቅስ፤ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ በጎ ተጽእኖ የሚፈጥር ነው ብለን እናምናለን። የ2013ን የስራ እንቅስቃሴ ስንገመግም፤ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንጂ፤ የምናሳየው የተገነባ ህንጻ፤ የሚቆረጥ ሪበን እንዳልሆነ አንባቢ እንዲረዳልን እንወዳለን። ይልቁንም፤ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮቻችን እና ለጋሾቻችን የራሳቸውን ነገርና የቤታቸውን ቀዳዳ ወደ ጎን ትተው ለሌሎች ለመድረስ ያደረጉት ጥረት ብዙዎችን ያነቃቃል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። የ2013 ስራችን፤ ብንተባበር ምን ማድረግ እንደምንችል ማሳያ፤ ለራሳችን የማናንስ እና የሌሎችን እጅ መጠበቅ እንደሌለብን እንደ ማንቅያ ትንሽ ምሳሌ እንዲወሰድ እንፈልጋለን። በተጨማሪም FICDO ከሚንቀሳቀስበት አካባቢ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው ብዙ መልካም ሰዎች ካላቸው ቆርሰው ከኛ ጋር ማካፈላቸው፤ ከዝያ ማህበረሰብ ለወጣን ምሳሌ የሚሆን፤ የበለጠ ቁጭትና መነቃቃት የሚያመጣ፤ ልዩነቶቻችንን ከመቁጠር ይልቅ በጋራ ነገሮቻችን ላይ በአንድነት እንድንሰራ የሚያደርግ ነው ብለን እናምናለን። ፈጣሪ ቢፈቅድ አብረን የበለጠ እንሰራለን።



# Get to know FICDO

# 1

# A BRIEF HISTORY ABOUT THE FOUNDING OF FICDO

**adapted from an interview by Comhlamh**

*At the end of 2017, Ewnetu Ermias, an IT professional took a career break to pursue a volunteering opportunity in Ethiopia. This experience spurred his desire for change, resulting in the founding of FICDO.*

Ewnetu's volunteering experience commenced in his home town of Fitche, central Ethiopia when he returned as a volunteer after two decades of living in Europe. He observed that not much had changed in his home town. Despite the abundance of natural and human resources, poverty is still rampant. Many vulnerable elderly are not only poverty stricken but also suffer from loneliness. Young girls and boys are not attending school for lack of basic resources. In most cases, children as young as seven and eight have to work to support their guardians or other family members. Ewnetu admits that what he saw was not new to him as he grew up in poverty himself. "But," he recalls, "my parents sacrificed everything and gave me an opportunity to go to school". He knows what it means to get an opportunity.

Ewnetu realized that the situation on the ground was overwhelmingly challenging, but he also believed that small hope-filled acts of kindness could improve people's lives. Hence, he started engaging with like-minded people, visiting the most marginalized within the community, the elderly. This kick-started an informal "befriending" service which caught the attention of others in the community. Ewnetu recalls,*"...wherever we went and started speaking about poverty in our community, we saw a strong support and willingness to change the status-quo"*. It seemed many people were aware of the social and economic challenges but did not know how to respond as an individual. However, this is not to say that there were no naysayers. Discouraged by past negative experiences and failed efforts, some were cautious about the new initiative.

Throughout the first half of 2019, the small group who were determined to see change pushed forward and built relationships with community members in Addis, who have been informally organised for a similar cause. In June 2019, a non-profit organisation called FICDO (*Fikir* Integrated Community Development Organisation) was formed and registered. The organisation is completely volunteer-led and run by local community members.

FICDO's core belief is that, with proper support and an enabling environment every community has what it takes to transform and flourish. The goal, therefore, is to embed mutual caring into the everyday life of the community. After all, for transformation to be sustainable, it has to come from within and be embraced by the community.

የFICDO ምስረታ መነሻው በመስከረም 2011 አቶ እውነቱ ለበጎ ፈቃድ ስራ ወደ ትውልድ ስፍራቸው ከመምጣት ጋር የተያያዘ ቢሆንም፤ በአዲስ አበባ የሚገኙ የአካባቢው ተወላጆች ሃሳቡ እውን እንዲሆን ከፍተኛ ርብርብ አድርገዋል። ድርጅቱ ከመመስረቱ በፊት፤ ካለፈባቸው ፈተናዎች አንዱና ዋነኛው "ከዚህ ቀደም ተጀምረው በአጭር እንደቀሩት፤ ይሄም የትም አይደርስም" የሚል አመለካከት ያላቸው ሰዎች መኖራቸው ነበር። ነገር ግን፤ ባለፉት ነገሮች ተስፋ ሳይቆርጡ "የቻልነውን እናደርጋለን" ብለው የተነሱ ሰዎች ድርጅቱ እንዲመሰረት ትልቅ ምክንያት ሆነዋል። ዛሬ ይህ ከድርጅታችን ታሪክ ጋር እንዲታወስ የምንፈልገው፤ ስራውን የሚሰራውም ሆነ የሚሰራለት ማህበረሰባችን በመሆኑ፤ የድርጅቱ ህልውና ከማህበረሰባችን ድጋፍ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ለማስመር ነው።

# FICDO GOALS

## አላማዎች

---

**"To say that on a daily basis you can make a difference, well, you can. One act of kindness a day can do it."**

Betty Williams

---

1. To promote positive community values by facilitating volunteering and sponsorship programs.

2. To support disadvantaged children with basic needs so that they break out of the poverty cycle.

3. To reconnect the marginalized and impoverished elderly with society that they might experience love and hope for the remainder of their lives.

4. To empower the community through education and awareness creation.

5. To rehabilitate and empower women engaged in prostitution due to lack of opportunities.

1. የማህበረሰባችንን የእርስ በእርስ የመረዳዳትና የመደጋገፍ መልካም ባህል የበለጠ ለማዳበር ፤ ህብረተሰባችንን ማስተሳሰርና የበጎ ፈቃድ አገልጋዮችን ማፍራት

2. በተለያዩ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጫናዎች የተነሳ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የተገደዱ ወይንም በአግባቡ መከታተል ያልቻሉትን ህጻናትና ወጣቶች አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ትምህርታቸውን ማስቀጠል

3. ከእድሜ መግፋት፤ ከጤና እጦትና የተለያዩ የኢኮኖሚ ጫናዎች የተነሳ በብቸኝነት እና በከፋ ድህነት የሚማቅቁና ቤተሰብ የሌላቸው አረጋዊያን ቀሪ እድሜያቸውን በሃዘን እና ተስፋ መቁረጥ እንዳያሳልፉ ፍቅር መስጠትና የተቻለውን ድጋፍ ማድረግ

4. ማህበረሰባችን ራሱን በራሱ እንዲያግዝ፤ እንዲነቃቃና በአብሮነት ለልማት እንዲነሳሳ ብሎም ችግሮቹን እንዲፈታ ግንዛቤ ማሳደግ እና የአመለካከት ለውጥ ላይ መስራት

5. በግንዛቤ እጥረት፤ በስራ አጥነት ወይንም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ተገደው እንደ ሴተኛ አዳሪነት ባሉ ያልተፈለገ ህይወት ለሚኖሩ ወጣት ሴቶች ስራ መፍጠር የሚችሉበትን ዕድል ማመቻቸት

---

**"ልዩነት የሚያመጣ ህይወት በየቀኑ መኖር ይቻላል? አዎን!
በየቀኑ አንድ ግዜ እንኳን ቸርነት ቢያደርጉ ልዩነት ፈጣሪ ነዎት"**

## VISION

A society where the physiological and psychosocial needs of all people are met that they may live a wholesome life.

## MISSION

We believe that kindness exists in each person and society. Our mission is to tap into this kindness and channel it into sustainable humanitarian and development efforts through social inclusion projects.

## VALUES

### LOVE

- We are motivated by love to serve others before ourselves.
- We believe in the transformative power of love. Hence we encourage and emphasise on serving in love

### HOPE

- We have high hopes that if we are united and serve each other in love, we can bring about positive changes in our community.

### HUMILITY

- We recognize that everyone has something to offer; hence we are willing to listen and learn

### INTEGRITY

- We practice what we preach...that is love (*fikir*).

### COURAGE

- We acknowledge the multi-faceted challenges our communities face. But, we are committed to face them.

### RESPECT & INCLUSIVENESS

- We treat and serve everyone, without exception, equally and respectfully.

## ራዕይ/ግብ

ለበጎ ስራ የተነቃቃና በመተጋገዝ አካባቢውን ምቹ የመኖርያ ስፍራና የፍቅር ምሳሌ ያደረገ፤ ከዚህም የተነሳ ሁሉም የማህበረሰቡ ክፍሎች መሰረታዊ ፍላጎቶቹ የተሟሉለት ጤናማ ህብረተሰብ ማየት

## ተልዕኮ

የበጎ ስራን እና የመረዳዳት ባህላችንን መሰረት ያደረጉ ራስ አገዝ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በውስጣችን እምቅ ሃብት እንዳለ በተግባር ማሳየት፤ ለማህበረሰባችን እና ለአካባቢያችን ለውጥ ሁሉም እንዲነሳሳ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት

## እሴቶቻችን

### ፍቅር

- ለህዝባችን ባለን ፍቅር እና ቅንአት ተነሳስተን እራሳችንን ሳይሆን ሌሎችን እናገለግላለን
- በፍቅር የተነሳሳ ልብ የራሱንም ሆነ የሌሎችን ህይወት የመለወጥ ሃይል እንዳለው እናምናለን። ስለዚህ ማንም መልካም ልብ ያለው ሰው፤ የበጎ ፈቃድ አገልጋይ በመሆን የድርጅታችን አጋር እንዲሆን አናበረታታለን፡

### ተስፋ

- ተባብረን እና በፍቅር ተሳስረን ከተጋን የህዝባችን ኑሮ ይለወጣል፤ አካባቢያችንም ይለማል የሚል ብሩህ ተስፋ ሰንቀን እንሰራለን።

### ትህትና

- ማንንም አንንቅም። ለአካባቢያችን መለወጥ ፤ ሁሉም ሰው የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዳለ እናምናለን።

### ታማኝነት

- እንደስማችን ፍቅርን በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር ኖረን እናሳያለን።

### ቁርጠኝነት

- አካባቢያችን ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች (ኋላ ቀርነት፤ ድህነት፤ ስራ አጥነት ወዘተ) ተስፋ አያስቆርጡንም።

### አክብሮት እና አካታችነት

- ሁሉንም ሰው በእኩል አይን፤ ያለ አድልዎ እና በአክብሮት እናገለግላለን።




# EDUCATION PROGRAM

## የትምህርት ፕሮግራም



2

# ABOUT FICDO'S EDUCATION PROGRAM

## ጥቂት ስለትምህርት ፕሮግራማችን

Several children in developing countries must start working from a young age to support themselves and/or even, at times, other family members. Hence they don't go to school. This is no different in the community that FICDO serves. Therefore, one of FICDO's strategic objectives is supporting such children with their basic needs (including food) and ensuring their education. However, feeding several children on a daily basis for an organisation with a meager budget is challenging. Therefore, as done in the previous year, we sought local solutions for these local problems; i.e. pooling every resource in the community to drive the cost low:

- The local authority donated an old building, which we use for storage and dining
- The local authority donated firewood for cooking
- We built a make-shift kitchen
- Two cooks were hired to prepare meals
- We source cheap ingredients locally
- Volunteers run the day to day activities
- Children get meals (breakfast and lunch) before heading to school

We also provide school uniforms, footwear and school supplies for the children.



ሃገራችንን ጨምሮ በብዙ ታዳጊ አገሮች፤ ብዙ ህጻናት እንደሌሎች እድሜ እኩዮቻቸው ትምህርት ቤት ከመዋል ይልቅ የእለት ጉርስ ፍለጋ ይባዝናሉ። የFICDO አንዱ አላማ ህብረተሰቡን እና ቅን ልብ ያላቸውን ሁሉ በማስተባበር ለእንደነዚህ ልጆች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ሁኔታዎችን (ምግብ ማግኘትን ጨምሮ) ማመቻቸት ነው። ነገር ግን በጥቂት ቅን ግለሰቦች እርዳታ የሚሰራ ድርጅት ቀርቶ ለሌላውም በየቀኑ ህጻናትን ምግብ ማብላት የማይታሰብ ነው። ለፈጣሪ ምስጋና ይግባውና፤ ይህ ችግር ሳያቆመን፤ የአካባቢያችንን ችግር ለራሳችን መፍትሄ በማበጀት ልክ እንደ 2012 ባሳለፍነው አመትም ያሰብነው ተሳክቶልን ልጆቻችንን መግበናል።



**FICDO እንደምን በትንሽ ወጪ ልጆችን አመቱን በሙሉ እንደመገበ እንንገርዎት፡**

- የአካባቢው ህዝብና እንደ እርስዎ ያሉ ቅኖች የሚሰጡንን አብቃቅትን አስቤዛ እንሸምታለን
- ሁለት አብሳዮች ቀጠርን፤ ማብሰያ ቦታ በአሮጌ ቆርቆሮ ሰራን
- ማገዶ እና መመገብያ ስፍራ የፍቼ 02 ቀበሌ በነጻ ሰጠን
- ይሄን ሁሉ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞቻችን ያለመሰልቸት በነጻ ይሰራሉ
- ህጻናት ቁርስና ምሳ በልተው ወደትምህርታቸው ያለሃሳብ ይሄዳሉ
- አቅም ለሌላቸው አረጋዊያንም ከዚሁ ምሳ እንቋጥራለን
- እግዚአብሄር ስራውን ባረከው፤ጸጋም አበዛልን

ከዚህም በተጨማሪ ህጻናት፤ ዩኒፎርም የትምህርት መርጃ መሳርያዎችና የማህበረሰብ ጤና አገልግሎት ድጋፍ ያገኛሉ።

# Quick Facts about Children in FICDO's Education Program

## በ FICDO የትምህርት ፕሮግራም የታቀፉ ህጻናት መረጃ




Guardians have no steady Income
**ቋሚ ገቢ ከሌላቸው አሳዳጊዎች ጋር የሚኖሩ**




One or both parents absconded
**ወላጅ ጥሏቸው የጠፋባቸው**




One or both parents passed away
**ወላጅ አባት ወይም እናት የሞቱባቸው**

FICDO's Education Program supports children from disadvantaged families. Of these, more than half are either raised by single parents or close relatives who have little or no disposable income of their own. One or both of parents of 25% of the children have absconded (mostly due to mental illness). The Program not only ensures the children's future through education, but also provides much needed daily meals required for their survival. Thank you for being our partners in changing lives.

**በ*FICDO* የትምህርት ፕሮግራም የታቀፉትና የትምህርት መርጃ መሳርያዎች፤ ዩኒፎርም እና የቁርስ እና ምሳ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሁሉም ህጻናት አሳዳጊዎቻቸው ቋሚ ገቢ ስለሌላቸው በከፋ የኑሮ ችግር ውስጥ ያሉ ናቸው። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አንድ ወይም ሁለቱም ቤተሰቦቻቸውን በሞት ያጡ ናቸው። ቀላል ቁጥር የሌላቸው ደግሞ ቤተሰቦቻቸው የት እንዳሉ ስለማይታወቅ ጎረቤት ወይም የሩቅ ዘመድ ያሳድጋቸዋል። እነዚህ ህጻናት፤ በርስዎ ድጋፍ የትምህርት እድል ብቻ ሳይሆን፤ ለህይወት እጅግ አስፈላጊ የሆነ ምግብ ጭምር ያገኛሉ።**

**There is no small donation. Every little helps.**

የአቅምዎን ቢረዱ፤ ለብዙ ህጻናት እንደርሳለን። ልግስና በረከት ነው፤ ቸርነት በማድረጉ የደኸየ የለም።

**የባንክ ሂሳብ ቁጥራችን፡**

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**
**1000287498474፤**
**ፍቼ ቅርንጫፍ**

**FICDO (ፍቅር የተቀናጀ የማህበረሰብ ልማት ድርጅት) በአዋጅ ቁጥር 113/2011 በመዝገብ ቁጥር 4207 በኢፌድሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጄንሲ የተመዘገበና በበጎ ፈቃደኞች የሚመራ ሃገር በቀል ድርጅት ነው።**



# BACK TO SCHOOL CHECKLIST

## ለትምህርት ቤት መከፈት ዝግጅት

As in all parts of the world, back to school time is busy for all parents. There is a rush to get school supplies, uniforms and all the essentials necessary for their children to start school. It is the same for FICDO's volunteer leaders too. In the picture below, tailors are invited to take measurements for our children's school uniforms.

- School Uniforms
- Footwear
- Stationery
- Volunteer Timetable
- Supplies for meals






ማንኛውም ቤተሰብ ትምህርት ቤት ከመጀመሩ በፊት ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ግብአቶች ለማሟላት እንደሚሯሯጥ፤ የFICDO የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች በአመቱ መጀመርያ በስራ ይጠመዳሉ። ለልጆች ዩኒፎርም ከማሰፋት በተጨማሪ፤ ለምገባው የሚሆን እህል ሸመታ፤ ማብሰያ እቃና ቦታ ማዘገጃጀት፤ እንጨት ማስጫን ወዘተ። በአመቱ መጀመርያ ልጆቹን ለትምህርት ቤት ለማዘጋጀት ደፋ ቀና የሚል ቤተሰብ፤ ዝግጅቱ የሚጠይቀውን በደምብ ይረዳዋል ብለን እናስባለን። የራሳቸው ትዳርና ኑሮ እያላቸው የሌሎችን ቀዳዳ ለመሸፈን በነጻ እንዲህ ደፋ ቀና ለሚሉ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞቻችን ከፍተኛ አድናቆትና ምስጋና አለን። እግዚአብሄር ያክብራችሁ፤ እናንተ የሌሎችን ቤት እንደምትሰሩ፤ ፈጣሪ የናንተን ቤት ይስራ እንላለን። ይሄንን ፕሮጀክት በገንዘብ እና በሞራል እየደገፋችሁ ያላችሁትም ፈጣሪ ወሮታችሁን ይክፈል እንላለን፤ እያደረጋችሁት ያላችሁት ቸርነት በእነዚህ ህጻናት ህይወት ውስጥ ትልቅ ትርጉም አለው።







# MAKING THE BEST USE OF LOCAL RESOURCES

## "የሃገሩን ሰርዶ በሃገሩ በሬ"

One of the greatest aspects of FICDO's community initiative is that we make the best use of local resources. Fitche Town administration donated to FICDO, a building previously used as a class room for pre-school children. The building has chairs and tables and is perfect to seat the children during meals. However, it lacked sufficient space for cooking. Undeterred by this challenge, our hardworking volunteers rose up to the occasion and sought to resolve the issue by constructing a makeshift kitchen in a small space behind the building. Within a few days, the kitchen was ready for use. Our volunteers also collect and recycle anything they get their hands on including worn furniture shown on the left hand side. Nothing is put to waste by this resourceful team!

የFICDO የምገባ ፕሮግራም፤ አንድ ማህበረሰብ በአንድ ልብ ለአንድ አላማ ሲቆም በአካባቢው ያገኘውን ነገር ሁሉ በመጠቀም ምን ያህል ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል አመላካች የሆነ ትንሽዬ ግን ውብ ፕሮጀክት ነው። የፕሮጀክቱን ጠቀሜታ ከማንም በላይ የተረዳው የፍቼ 02 ቀበሌ አስተዳደር ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የመመገብያ ስፍራ እና ቁሳቁስ ለገሰ። ክፍሉ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች የተሟሉለት ቢሆንም ትንሽ ማጸዳዳት ያስፈልገው ስለነበር፤ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞቻችን ይህንን አደረጉ። ግን የማብሰያ ቦታና አስቤዛ ማስቀመጫ አልነበረውም። ለዚህም የበጎ ፈቃድ ሰራተኞቻችን መፍትሄ አበጁ፤ ያረጁ ቆርቆሮዎችን ሰብስበው ኩሽና ሰሩ። የተጣሉ እንጨቶችን፤ ቁምሳጥን ወዘተ ጠጋግነው በስራ ላይ አዋሉ። "በጀት ስለሌለን ፤ ይህ እና ያ ስለጎደለ አንችልም" ብለው ተስፋ ሳይቆርጡ ፤ ምንም ነገር ሳይንቁ፤ ባለቸው ነገር አብቃቅተው እና ዘይደው ይኸው አመቱን ሙሉ ማህበረሰቡን አገለገሉ። የሃገሩን ሰርዶ በሃገሩ በሬ ያልነው ለዚህ ነው። ለብዙ ችግሮቻችን ከኛው መሃል መፍትሄ አይጠፋም። ሌሎችን ከመጠበቅ ይልቅ፤ የቻልነውን ማድረግ ትልቅ ጥበብ ነው።

በዚህ አጋጣሚ፤ የፍቼ ከተማ አስተዳደር አካላት ፤ለFICDO የስራ እንቅስቃሴዎች እያሳያችሁ ላላችሁት ሁለንተናዊ ድጋፍ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ለዚህ አገልግሎት በተለያየ መንገድ በመሳተፍ እገዛ እያደረጋችሁ ላላችሁ የህብረተሰባችን ክፍሎች እና የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

# SERVING WITH COMPASSION

## በርህራሄ የተሞላ አገልግሎት

At the heart of FICDO's service is compassion. The team recognizes that the daily meals children get from our feeding center means so much to them and their families. These may be the only meals they get for the day as several parents/guardians may not afford to put food on the table. Hence, beyond ensuring the children's continuous school attendance, these meals are essential for their survival. Recognizing this fact, meals were provided even during short school breaks. We are grateful to our volunteers for their care and love for these children, and to our donors and friends for supporting this worthy cause.

የFICDO አገልግሎት የማህበረሰባችንን መሰረታዊ ፍላጎቶች ከግምት ያስገባ የፍቅር አገልግሎት ነው። በምገባ ፕሮግራሙ የሚጠቀሙ ህጻናት፤ እለት እለት የሚያገኙት ቁርስ እና ምሳ ምን ያህል እንደሚያስፈልጋቸው የበጎ ፈቃድ አገልጋዮቻችን ይገነዘባሉ። ምናልባትም ከህጻናቱ አንዳንዶቹ በቤታቸው በቀን ሶስት ግዜ ላይመገቡ ይችላሉና። ስለዚህ ይሄ ፕሮግራም ልጆቹ ትምህርት ላይ እንዲያተኩሩ ከመርዳት ባሻገር፤ ለህይወታቸው የሚያስፈልጋቸው አንዱና ዋነኛውን መሰረታዊ የሆነውን የምግብ ፍላጎት ማሟላት ነው። ይህን ከግምት በማስገባት፤ ትምህርት ቤት በግማሽ ሴሚስተር ላይ ለአጭር እረፍት ሲዘጋም እንኳን፤ አገልግሎቱን አላቋረጥንባቸውም።

ለFICDO የበጎ ፈቃድ ሰራተኞችና አስተባባሪዎች፤ እንዲሁም ይህንን ፕሮጀክት በገንዘብና በሞራል ለምትደግፉ ሁሉ አድናቆታችንን ልንገልጽ እንወዳለን። እግዚአብሄር ይባርካችሁ።



# INVESTING IN THE FUTURE

## ትውልድ ላይ በእምነት እና በተስፋ መዝራት



The environment in which many of our children are growing is harsh. But we are sowing seeds of hope, by faith, that our small actions would bear fruit. By investing on the children's education, we are investing in their future. We are exercising pro-active care. We hope that the children break out of the crushing poverty that has had weighed down on their parents and generations before them.

ብዙ የማህበረሰባችን ልጆች እጅግ አስቸጋሪ ወደሆነ ህይወት ይወለዳሉ፤ ከእድሜያቸው በላይ በሆነ መከራ ውስጥ ያልፋሉ። በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በእምነት እና በተስፋ ዘር እንዘራለን። ይህቺ ዘር አንድ ቀን በቅላ ታፈራለች በሚል ተስፋ። ልጆች የትምህርት እድል እንዲያገኙ የተቻለንን ሁሉ የምናደርገው፤ የወደፊት ኑሮአቸው እንዲሻሻልና ቤተሰቦቻቸውን እና የቀደመውን ትውልድ ካጎበጠው ድህነት ቀንበር እንዲላቀቁ ነው። ትውልድን ከድህነት እናስመልጥ።

MSW is seven. Her father passed away when she was one. Her mother is visually impaired and lives off street begging. For MSW and her siblings, attending school is unthinkable since getting a daily meal is a priority. Hence, MSW's elder sister is working as daily labourer to supplement the family income. MSW's fate would not be any different.



Thanks to FICDO's education program, MSW has been enrolled in a nearby primary school since last year. FICDO covered her expenses including school materials and a uniform. Above all, she gets two meals a day from our feeding program. She is now in 1st class and thriving.

MSW የ7 አመት ህጻን ናት (ፊቷን ያላሳየነው ሆን ብለን ነው)። አንዲት ታላቅ እህት እና አንድ ወንድም አላት። አባቷ ከዚህ አመት በሞት የተለዩ ሲሆን፤ እናቷ ደግሞ ማየት የተሳናቸው ስለሆነ የራሳቸውን እና የ3 ልጆቻቸውን ህይወት ለማቆየት ልመና ላይ ተሰማርተዋል። የMSW ታላቅ እህትም የቤተሰቡን ኑሮ ለመደጎም በቀን ስራ ላይ ተሰማርታለች። እንደ MSW ላሉ ልጆች፤ የእለት ጉርስ ማግኘት ራሱ ከባድ ፈተና በመሆኑ፤ትምህርት ቤት መሄድ እንደ ቅንጦት ነው።

ለፈጣሪ ምስጋና ይብዛና፤ MSW ከአምና ጀምሮ በFICDO እርዳታ ትምህርት ቤት ተመዝግባ ዘንድሮ የ1ኛ ክፍል ተማሪ ነች። ቢያንስ በቀን ሁለት ግዜ ምግብ ታገኛለች፤ ትምህርቷንም ቀጥላለች። ባለን አቅም የምንችለውን ለማድረግ ተረባርበን፤ በእግዚአብሄር ጸጋ እና በርስዎ እገዛ ብዙ እንደ MSW ያሉ ህጻናትን ህይወት ልንታደግ እንችላለን።

# FROM EUROPE WITH LOVE

*Shem Romanowiski is originally from Poland. He now lives and works in Dublin, Ireland. Shem has been our monthly supporter of FICDO's Education Program for over a year. We convinced Shem that his story will inspire our readers and supporters. So he kindly agreed for an email interview. Nuhamin Ermias has compiled his responses as follows:*



Shem

**FICDO: How did you hear about FICDO?**
**Shem:** I first heard about FICDO from Ewnetu about a year and half ago (winter 2019/2020) when we were volunteering for a charity in Dublin. Ewnetu told me about FICDO and its social inclusion projects supporting communities in central Ethiopia, especially children by providing breakfast and lunch as well as school materials and uniforms. As I am already a project coordinator with another organisation providing social inclusion projects to immigrants in Ireland, I immediately let Ewnetu know I wanted to get involved with FICDO.

**FICDO: What made you decide to reach out to children in Ethiopia through FICDO?**
**Shem:** I am originally from Poland and arrived in Ireland in 2004 in search of a better life. I experienced difficulties in accessing jobs in Dublin because I didn't have a good education. Through my personal experience, I can say that education improves lives, broadens horizons and brings wealth and progress to the individual, his/her family as well as to the community. I always wanted to support children in an African country by helping a small, grassroot organisation. With this in mind, FICDO became the organisation of my choice and I am delighted to be able to support children in central Ethiopia.

**FICDO: Your support not only ensures the wellbeing of a child through provision of basic daily meals but also gives educational opportunities for children to break out of poverty. How does that make you feel/affect you?**
**Shem:** As mentioned above, I truly believe the only way out of poverty is through education. Knowing that there would be a child that will receive an opportunity for education is very important to me and I am glad I can support FICDO in its effort to deliver this promise to children that it serves.

**FICDO: How do you know that your money is well-spent (goes to the right place)?**
**Shem:** I was reassured by Ewnetu that donated money are spent directly in the community. Also, there is an annual newsletter as well as Ewnetu's posts and updates on Facebook where I can inform myself about the developments of the project.
But also, it would be great to know more about the children that receive support; their names, their family circumstances etc. That way closer ties could be established.*

**FICDO: Any message for the community and the children that you are supporting?**
**Shem:** I just hope the children avail of every opportunity to learn and discover. Never stop dreaming and be brave! I hope to see you very soon!

*Note from FICDO: *All donations go to services we provide for children and elderlies under our care. We have no overhead costs as we are volunteer run and have no paid staff so far. Since some of the services that we provide are labor intensive, our volunteers dedicate their times exclusively on those. Lack of resources means we do not have dedicated staff and social workers who could facilitate/manage sponsor-child interactions on a regular basis. Resources permitting, we intend to move in that direction in the near future. For the time being, we use social media and e-zines to update our supporters.*

# SOUL-2-SOUL PROGRAM

ፍቅር ለአረጋዊያን



**Imparting love, renewing hope, connecting people to people**

# ABOUT SOUL-2-SOUL PROGRAM

## ጥቂት ስለ "ፍቅር ለአረጋዊያን" ፕሮግራማችን

Millions of men and women who are engaged in casual and unpredictable employment for all of their adult life are less likely to have pensions or savings in their old age. Usually, extended family members support such elderly persons. However, those who have no close family often live in dire conditions. In addition to material poverty, the elderly can also suffer from loneliness. FICDO's *SOUL-2-SOUL* program is designed to address these issues:



- We strive to mobilise the community to befriend elderlies who have no family. The idea is connecting one person to another, hence we named the program *SOUL-2-SOUL*.
- We also strive to connect those who have limited or no income, and struggle to get daily meals for survival, with sponsors who may support them with their financial needs. For those who have no sponsor, we try to provide small monthly cash supplements.
- For those with mobility issues due to ill-health and old age, who may not be able to prepare meals for themselves, we do our best to bring packed lunch (usually from the little excess at the school feeding program that we are running).
- We do community sensitization and advocacy, highlighting not only issues the elderly are facing but also the fact that they deserve a life of dignity

ዘመናቸውን በቤት ሰራተኝነት እና በቀን ስራ ተቀጥረው የሚኖሩ ብዙ ወገኖች አቅማቸው ሲደክም የሚተዳደሩበት በቂ መጦርያ የማጠራቀም እድላቸው አነስተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም የሚያገኙት ከቀን ተቀን ማኖርያ ፈቅ አይልምና፡፡ እድለኛ ሆነው ልጆች ያደረሱ፤ ልጆቻቸው ይጦሯቸዋል፡፡ ልጆች ወይም የቅርብ ዘመድ የሌላቸው ግን ህይወታቸውን ለማቆየት እስከ መንገድ ዳር ልመና ድረስ ይደርሳሉ፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፤ከእርጅና እና ጤና ችግር የተነሳ መንቀሳቀስ አቅቷቸው ማንንም ሰው ሳያገኙ፤ ሰው በሞላበት ሃገር በብቸኝነት ሊማቅቁ ይችላሉ፡፡ በድርጅታችን “ነፍስ-ለነፍስ” /soul-2-soul/ ብለን በምንጠራው እና አረጋዊያንን ያማከለ አገልግሎት፤ እነዚህን ችግሮች በተቻለ አቅም ለመቅረፍ እንጥራለን፡

- አስታዋሽ የሌላቸው አንድ አረጋዊ፤ በወር አንድ ቀን እንኳን ግማሽ ሰአት ሰጥቶ የሚጎበኛቸው እና የሚያዋያቸው ሰው ቢያገኙ ቀላል አይደለም፡፡ አረጋዊያን በመጨረሻ የህይወት ዘመናቸው በሃዘን እና በብቸኝነት እንደተቆራመዱ፤ ሁላችንም ወደማንቀርበት ቦታ እንዳይሄዱ የአቅማችንን በማድረግ፤ ፍቅር በማሳየት ተስፋቸው በጥቂቱም እንዲታደስ ከበጎ አድራጊ ሰው ጋር እናገናኛቸዋለን ፡፡ አንድ ነፍስ ለሌላዋ ነፍስ እንድትደርስ!
- የእለት ጉርስ ለማግኘት ተቸግረው በከፍተኛ የኑሮ ጫና ውስጥ ላሉት፤ የቻሉትን ያክል የሚደጉሟቸው ስፖንሰር እናፈላልግላቸዋለን፡፡ ስፖንሰር ላላገኙ አረጋዊያን የኑሮ ድጎማ እንድትሆን በየወሩ 500 ብር እንሰጣቸዋለን፡፡
- ምንም አይነት ብርም ሆነ ሌላ ቁሳቁስ ቢያገኙም ከጤና እጦት የተነሳ ምንም ማድረግ ለማይችሉ፤ በቻልነው አቅም ለተማሪዎች ምገባ ከምናዘጋጀው ምግብ ምሳ እንቋጥርላቸዋለን፡፡
- አጋጣሚ ባገኘን ሁሉ አረጋዊያን ያለባቸውን ፈተና ብቻ ሳይሆን፤ ክብር ልንሰጣቸው እንደሚገባ ድምጽ እንሆናቸዋለን፡፡

አረጋዊያን ከገንዘብ እና ቁሳቁስ ድጋፍ በላይ ሰው ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህ ህልማችን፤ በጤና እና በተለያዩ ችግሮች ቤት የቀሩ፤ ምንም ረዳት እና ጠያቂ የሌላቸው ወገኖቻችንን ከህብረተሰቡ ጋር በማገናኘት በፍቅር ማገልገል፤ ባይወልዱንም "ልጆች" እንድንሆንላቸው ህብረተሰቡን ማነሳሳት ነው፡፡ የምንሰጣቸው ብዙ ነገር በእጃችን ባይኖርም ፍቅር እንስጣቸው። እርስዎም ይህንን ማድረግ ይችላሉ። ኑ፤ አብረን መልካሙን ስራ እንስራ።



# A LIFE OF DIGNITY

Most people, including the elderly, want their independence and would do anything to support themselves.  No one wants or chooses to live on handouts.  At the age of 96, Mr Z lives on his own and works hard to make ends meet. He is a traditional weaver, a proud man with unique skills and tenacity.  However, due to ill-health and old age he struggles to make enough to pay for his basic needs.

Thanks to one of our private donor, who supplements his income, Mr Z's life has become that of hope and gratitude.  Unsurprisingly, Mr Z got emotional when we asked him how he was getting on with life.  He marvels, "how did a family I have never met before do this for me? Surely that family must have been sent from God!".  It is such testimonies, that keeps the FICDO team going.  To sponsor an elderly like Mr Z with whatever you can, please email us at fikirintegratedcdo@gmail.com.

# "I owe my survival to your support..."

# " እናንተ በምትሰጡኝ እርዳታ ትንፋሼ ቀጥሏል..."



The above statement was that of one of the elderly person's under the care of FICDO's *SOUL-2-SOUL* program, which is enabled by our generous donors like Dr Tadesse Woldemariam's family.

Tadesse's family live in Addis. Tadesse himself is one of FICDO's trustees. After receiving the list containing the profiles of the elderlies selected for the *SOUL-2-SOUL* program, his family sponsored one elderly. However, after visiting and witnessing the dire condition in which the elderlies live, Tadesse's family would go on to donate a lump-sum. This donation supported ten elderlies for the entire 2020/21 budget year.

It is indeed such generous donations that help several elderlies in our communities cope with the harsh realities of poverty. We thank Tadesse's family for not only renewing the hopes of vulnerable elderlies but also inspiring us all.

ይሄ ከላይ ያለው የምስክርነት ቃል፤ በFICDO የታቀፉ አንድ አረጋዊ በቅርቡ ሊጎበኟቸው ለሄዱት የFICDO የቦርድ ሊ/መንበር የተናገሩት ነው፡፡ በእርግጥ ለእኚህ አረጋዊ ትንፋሽ መቀጠል ምክንያት የሆኑት፤ የFICDO "ፍቅር ለአረጋዊያን" ፕሮግራም እውን እንዲሆን የደገፉን እንደነ ዶ/ር ታደሰ ወ/ማርያም አይነት ቤተሰብ ያሉ ለጋሾች ናቸው፡፡

ዶ/ር ታደሰ እና ባለቤታቸው ስናፍቅሽ ኑራቸው አዲስ አበባ ሲሆን ከድርጅታችን ምስረታ ጀምሮ ለFICDO ከፍተኛ ድጋፍ እያደረጉልን ይገኛሉ፡፡ ዶ/ር ታደሰ የድርጅቱ የቦርድ አባልም ናቸው፡፡ በመጀመርያ የአረጋዊያኑን ፕሮፋይሎች በላክንላቸው ግዜ በርህራሄ ተነሳስተው አንድ ሰው ስፖንሰር አድርገውልን ነበር፡፡ ከተወሰነ ወራት በኋላ ደግሞ፤ ዶ/ር ታደሰ ለግል ጉዳይ ወደ ፍቼ ከተማ በተጓዙ ግዜ የአረጋዊያኑን የኑሮ ሁኔታ በአካል የመጎብኘት እድል አገኙ፡፡ በጉብኝቱ ወቅት ያዩት የአረጋዊያኑ አሳዛኝ አኗኗር ልባቸውን ስለነካው፤ ለድርጅታችን ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ አድርገውልናል፡፡ የዶ/ር ታደሰ ቤተሰብ የለገሱትን ገንዘብ ለአስር አረጋዊያን፤ በየወሩ ለአንድ አመት ያክል የገንዘብ ድጎማ ልናደርግላቸው ችለናል፡፡ የአረጋዊያን ተስፋ እንዲታደስ ምክንያት የሆኑትና ለብዙዎቻችን የፍቅር ምሳሌ የሆኑትን የዶ/ር ታደሰን ቤተሰብ እያመሰገንን፤ ሁላችንም በተቻለን አቅም ድጋፍ ለሚሹ ወገኖቻችን እንድንደርስ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

አረጋዊያንን በየወሩ ስፖንሰር ለማድረግ ወይም በቻሉት ግዜ የአቅምዎን ለመደገፍ በስልክ ወይም በኢሜል ያግኙን፡፡ ዛሬውኑ የቻሉትን ያክል ለመደገፍ፤ በሚቀጥለው የባንክ ቁጥራችን ገቢ ያድርጉ፡፡ የአረጋዊያኑን ኑሮ ሙሉ በሙሉ ባንለውጥም ፤ ትንሽ ቀዳዳ መድፈን እንችላለን፡፡

የባንክ ሂሳብ ቁጥር:
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፤ ፍቼ ቅርንጫፍ፤
የደብተር ቁጥር፡ 1000287498474



# COVID-19 RESPONSE

## አስቸኳይ እርዳታ





# RESPONSE IN A PANDEMIC

## የአስቸኳይ ግዜ እርዳታ

2020 was an exceptionally challenging year for many of us. Even in 2021, the Coronavirus has continued to impact on the way we live.
Although every community has been affected, some are more vulnerable than others. Efforts to contain the virus during the early days of the pandemic shocked the community that FICDO serves to the core. People needed to make a very hard choice between risking catching the virus by going out or going hungry by staying in. A climate of fear gripped the community. That was when FICDO started a pledge to collect donations to support the community. Thanks to your generous donations, throughout 2020 and early 2021 we could serve and save the lives of hundreds of people during those harsh times. Restrictions have since eased in 2021 and people have returned to work.

የኮሮና ቫይረስ በሃገራት ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ቀውስ እና የኑሮ ውድነትን ያስከተለ ሲሆን፤ ሃገራችንም ከዚህ አልተረፈችም። በተለይ በመጀመርያ አካባቢ ቫይረሱን ለመከላከል የተወሰዱት እርምጃዎች፤ ብዙዎችን ከፍተኛ የኑሮ ቀውስ ውስጥ ከቷቸው ነበር። በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙና ቀድሞውንም ኑሯቸው ከእጅ ወደ አፍ የሆኑ ወገኖቻችን ጦማቸውን እንዳያድሩ እርዳታ በማሰባሰብ፤ በ 4 ዙሮች ወደ 250ሺ ብር ግምት ያለው የአስቸኳይ ግዜ እርዳታ አድርገናል። ድጋፎቹ ከአካባቢያችን ማህበረሰብ፤ የንግድ ተቋማት፤ ግለሰቦች እና በውጭ ሃገር ካሉ ደጋፊዎቻችን የተገኙ ናቸው። ምንም እንኳን የቫይረሱ ነገር ባያበቃም፤ እግዚአብሄር ይመስገን አሁን ወጥቶ መግባት ተችሏል።



# COMPASSION IN THE AGE OF COVID-19

## የርህራሄና የፍቅር አጭር ታሪክ

When COVID-19 was first reported in Ethiopia, in March 2020, Rebecca Ewnetu was very much concerned for the children under FICDO's care.  She was stricken by a photograph showing anxious children attempting to cover their mouth with their hands for fear of catching the virus.  By then, little was known about the virus and what impact it would have on people of various age groups.



Rebecca teamed up with her school friend Olivia who had just set up a crafts business dedicated to hand making reusable face masks. Altogether the girls donated 120 euros worth of individually crafted masks which we then distributed to 30 children partaking in our education program.

We are greatly inspired by these two young girls' generosity and compassion. Let's remember that just as COVID-19 is contagious, so is compassion.  How did you impact your "neighbor" today? Were you compassionate?

ርብቃ እውነቱ በአየርላንድ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነች። የCOVID-19 ሃገራችን እንደገባ ሰሞን፤ በFICDO የታቀፉ ልጆች በአንድ ቪዲዮ ላይ ከፍርሃት የተነሳ በሚመስል መልክ፤ አፋቸውን በጃቸው ለመሸፈን ሲጨናነቁ ታያለች። ይሄ ለቀናት እንቅልፍ እንደነሳት ያወቅነው ከሳምንታት በኋላ ነበር።  "ለእነዚህ ልጆች፤ የፊት ጭምብል (ማስክ) መግዛት አለብኝ" ብላም ትወስናለች። ኦሊቪያ ከተባለች ጓደኛዋ ጋር በመሆን በበይነ መረብ አነስተኛ የጌጣጌጥ ንግድ በመጀመር ያገኙትን ገቢ በመጠቀም፤ ግምቱ 180 ዩሮ የሚያወጣ ማስክ ለግሰዋል።በግዜው ህጻናት ማስክ ባያደርጉም ችግር እንደማይኖር ስለማይታወቅ፤ እኛም ለትንንሾቹ ጭምር የፊት ጭምብሎችን (ማስክ) አከፋፍለናል። የእነዚህ ሁለት ወጣቶች ርህራሄ ልብ የሚነካ ሆኖ ስላገኘነው ታሪኩን አቅርበነዋል። በዚህ አጋጣሚ፤ ሁሉም ሰው ማህበረሰባችንን በሚጠቅም ዘርፍ የአቅሙን እንዲያግዝ እናበረታታለን።  ልብ እንበል፤ የCOVID-19 እንደሚተላለፍ ሁሉ በጎነትም እንዲሁ ነው። እኛ በጎ ብናደርግ፤ ልጆቻችን፤ ጎረቤቶቻችን እና የስራ ባልደረቦቻችን ሁሉ ይነቃቃሉ። በጎነት ይተላለፋል።



# HEALTH CARE SERVICE

## የጤና አገልግሎት

The **Community Based Health Insurance (CBHI)** scheme in Ethiopia is highly important as it aims to increase access to healthcare for the most destitute. It is heavily subsidized by the Government, with members expected to pay an annual premium of just seven euro per household. Unfortunately, even seven euro per annum can be too much to afford for the most vulnerable in our community. Taking this into account, FICDO has added "Health Care Service" as one of our core social inclusion projects. All elderly and children under FICDO's care are now covered. We thank our friends who stepped in to support this project.

በሃገራችን የግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አገልግሎት ማግኘት ለብዙዎች የሚታሰብ አይደለም። ስለዚህ፤ በከፍተኛ የመንግስት ድጎማ የሚደገፈው የማህበረሰብ የጤና መድህን አገልግሎት፤ ዝቅተኛ ገቢ ውስጥ ላሉት የማህበረሰባችን አባላት ያለው ጠቀሜታ እጅጉን የላቀ ነው። አንድን ቤተሰብ ለአንድ ድፍን አመት የጤና መድን ሽፋን ተጠቃሚ ለማድረግ ወጪው 310 ብር ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ምንም አይነት ገቢ ለሌላቸው፤ ይሄም ቢሆን ከባድ ነው። ይህንን ከግምር በማስገባት፤ በድርጅታችን የታቀፉት አረጋዊያን፤ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው የጤና መድን ሽፋን ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይህንን እንደ ቋሚ ፕሮጀክት ይዘናል። በዚህ አገልግሎት ከጎናችን ለመቆም ለተረባረባችሁ ሁሉ ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን።



# MOBILIZATION

## የማስተባበርና የማነቃቃት ስራ



# CELEBRATING FESTIVITIES TOGETHER

## አመት በአልን ከማህበረሰባችን ጋር

Christmas and Easter are two of the biggest holidays of the year in the communities that FICDO serves. On these days, people usually host lunch parties and celebrate the festivities with close friends and family members in their own home. These festive times are seasons of joy and celebration for many. However, some struggle with the harsh reality of deep poverty and loneliness. In solidarity with these members of our community, FICDO's volunteers host lunch parties for those we serve. We also invite city officials and other dignitaries to join the celebration so that everyone can sit together and enjoy the festive atmosphere. For those who are not strong enough to attend in person, our volunteers bring packed lunch. In this manner, we have committed to nurturing a community spirit.

አመት በአል በማህበረሰባችን ጨምሮ በመላው ሃገራችን በድምቀት ይከበራል። በአመት በአል፤ ሰው ሁሉ ከወዳጅና ዘመዱ ጋር ቤት ያፈራውን ይቃመሳል፤ ቀኑን በደስታ ያሳልፋል። ምንም ቤተሰብ ለሌላቸው አረጋዊያን እና ብቻቸውን ለሚኖሩ ሰዎች ግን አመት በአል የትካዜ እና የብቸኝነት ቀናቶች ሊሆኑባቸው ይችላሉ። አንዳች የሚቀመስ ከቤታቸው ለሌላቸው ደግሞ ሃዘኑ ድርብ ነው። ከዚህ የተነሳ፤ አመት በአልን ከምናገለግለው ህብረተሰብ ጋር መዋልን እንመርጣለን። ስለዚህ በየአመቱ፤ አቅም በፈቀደ መጠን ምሳ ደግሰን የምናገለግላቸውን እና የከተማችንን አስተዳደር ጨምሮ ሌሎች እንግዶችን ጠርተን አንድ ላይ እናሳልፋለን። በግብዣችን ትልቅ እና ትንሽ፤ ያለውና የሌለው ተብሎ ልዩነት የለም፤ ሁላችን አንድ ቤተሰብ ሆነን በአንድ ላይ ማዕድ እንቆርሳለን። ከአቅም እና ጤና ማነስ የተነሳ መምጣት ላልቻሉት በሳህን እናደርስላቸዋለን። በዚህ አገልግሎት፤ "የራሴ ቤተሰብ እና እንግዳ አለብኝ" ሳይሉ ከማህበረሰባችን ጋር ለማሳለፍ ለወሰኑ የበጎ ፍቃድ ሰራተኞቻችን እግዚአብሄር ይባርካችሁ እንላለን። ግብዣችንን ሳትንቁ ለምትገኙልንና እርስ በርስ እንድንያያዝ ምክር ለለገሳችሁን የከተማችን አስተዳደር፤ ባለሃብቶች እና ቅን ነዋሪዎች ልባዊ ምስጋና እናቀርባለን። ይህቺ ትንሽ ጅምር ከፍ ወዳለ መተባበር እና ቤተሰባዊ መተሳሰብ እንድታድግ የሁላችንም ህልም ነው። ለዚህም ጠንክረን እንሰራለን።







# PLANNING WITH THE COMMUNITY

## ከማህበረሰባችን ጋር ምክክር

Community mobilization is one of FICDO's core objectives. We started the year by holding a public consultation /community engagement event, during which key issues were identified and resourcing were discussed. Certificates were also handed to volunteers and key partners. We were encouraged by the various pledges, including a pledge by the community to cover the cost of the 2020/2021 academic year's stationery supply for all students in primary and secondary schools in the town. Seven representatives were also named during the gathering, to work with FICDO.



የFICDO ዋና አጀንዳ፤ የምናገለግለውን ማህበረሰብ (ግለሶቦችን፤ የግል እና የመንግስት ተቋማት፤ የመስተዳድር አካላት ወዘተ) ለበጎ ስራ በመቀስቀስ በከተማችን ማህበረሰብ ላይ አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት ነው። በዚህ መሰረት፤ 2013ን ከማህበረሰቡ ከተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ነው የጀመርነው። በእለቱም ከድርጅታችን ጋር በመተባበር ከማህበረሰባችን ጎን ለቆሙት የእውቅና ሰርቲፊኬት ከተሰጠ በኋላ፤ በአዲስ አመት ማህበረሰባችንን በመወከል የFICDO የስራ እንቅስቃሴ የሚመሩ የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች ተመድበዋል። በእለቱም ተሰብሳቢዎቹ፤ የFICDO የስራ እንቅስቃሴዎች እና ማህበረሰባችንን በሚችሉት ሁሉ እንደሚደግፉ ቃል ገብተዋል።



# THE UNSUNG HEROES OF OUR COMMUNITY

